የልጅነት አርሾ

የአላህ ችሮታ ሆነና የደዕዋ ሥራን በልጅነት ነው የጀመርኩት። አሁን ላይም በ‚ያንሰ በመስመሩ ላይ በመገኘቴና የአላህን ቃል ለመናገር በመታደሌ ዕድለኛ ነኝ ብዬ እስባለሁ። ገና አሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ሳንገባ ጭምር ያኔ አንድ ትልቅ ዳቦ አሥራ እምስት ሳንቲም በነበረ ጊዜ አሥር አሥር ብር እያዋጣን በከተማችን ዙርያ ወዳሉ ዮገጠር መንደሮች ከጓደኞቻችን ጋር በመሆን እንንቀሳቀስ ነበር። ሦስትም፣ አሥርም ሰላሳም ቀን ደዕዋ እንወጣ ነበር። "ኢንነ ፈላሐና ወነጃሐና..." የምትለዋን የኢዕላን ፎርማት ሁላችንም በቃላችን ሸምድደናት ነበር። ‹ኢዕላን› ማለት ማስታወቂያ ነው። ከመግሪብ ሶላት በኋላ ደዕዋ/ትምህርት ስለሚኖር ቁጭ ብላችሁ እንድታዳምጡ ለማለት ነው።

በርግጥ ያኔ ሰው ሁሉ ዲን የተጠማበት ጊዜ ነበር። የደዕዋ ልጆች መጡ! እያለ በየመስጊዱ ምእመን እንደ ቱሪስት ይከበን ነበር። ምንም የማያውቁ ልጆች ናቸው ብሎ ሳይንቀን መስጊድ ሞልቶ በተመስጦ ሲያዳምጠን ትዝ ይለኛል። በምንናገራቸው ነገሮችና በምናስተላልፋቸው መልዕክቶች ይገረማል። በርግጥም በኛም ሆነ በሌሎች ትላልቅ ዳዒዎች ይደረግ የነበረው የያኔው የደዕዋ እንቅስቃሴ ትልቅ በረካ ነበረው። ብዙዎች ሰልመዋል። ከመንገድ ጠፍተው የነበሩት በርካቶች ወደ ቀናው መንገድ ተመልሰዋል። በሥም ብቻ ሙስሊም የነበሩ በርካቶች ቁርአንና ሌሎች ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ተምረዋል።

ከፍ እያልን ስንሄድ የደዕዋ እንቅስቃሴው እየሰፋና እየሞቀ መጣ። እነ ሸህ ጀማል ሊደዕዋ ያሰማሯቸው የነበሩ ጀማዓዎች ድንቅ ሥራዎችን ሠርተው አሳይተውናል። ሸህ ጀማል መላ ሕይወታቸውን ለደዕዋ ሥራ የሠጡ ሰው ነበሩ። "ሸህ ጀማል ደዕዋ" በሚል የቅጽል ሥማቸው በሰፊው ይታወቃሉ። ይህንኑ ሥማቸውን ይዘው መቃበር ወረዱ -አላህ ይዘንላቸው። የሰው ልጅ በኖረበት ሥራ ላይ ይሞታል፤ በሞተበት ነገር ላይም ይቀሰቀሳል። ሸህ ጀማል የሌት ተቀን ሃሳባቸውና ጭንቀታቸው የሰዎች መስተካከል ነበር። አይደለም የአንድ አካባቢ ሰው፣ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ሊስተካከል ሰለሚችልበት ሁኔታ ይጠበቡ ይጨነቁ ነበር። ደዕዋ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢ በማጥናትና በማስጠናት በርሳቸው አሰማሪነት የደዕዋ ሰዎች ወደ አንድ የተወሰነ አካባቢ በመንቀሳቀስ ሙሉ መንደር ይዘው እዚያው ከርመው ዲን አስተምረው ይመለሱ ነበር። ከፊሉን ደግሞ የዲን ግንዛቤ አናሳ ወደሆነበት አካባቢ በመላክና ታዋቂ

ሰዎቻቸውን አሳሳ ወደሚገኘው ዋና መርከዝ በማምጣት እዚያ ቆይተው ዲን እንዲማሩ ያደርጉ ነበር። የሆነ ጊዜ 'ኮኮሳ' ከሚባል ራቅ ያለ አካባቢ ሰባ የሚሆኑ ትላልቅ ሰዎች በእግር አሳሳ ድረስ መጥተው ዲንን ተምረው ተመልሰው አገራቸው ገብተው ሃይማኖታቸውን እንዳስፋፉ አስታውሳለሁ። ሌላው ማጎበረሰብ ደግሞ አሳሳ ድረስ ይመጣና የደዕዋ ቡድን አሊያም የዲን አስተማሪ እንዲላክለት ይጠይቅ ነበር። የያኔው ዘመን አንዳንዱ በርግጥም የሶሐባን ዘመን ይመስል ነበር።

ከልጅነት ዕድሜ ከፍ እያልን ስንሄድ ተበታተንን። እኔም በቂርኣትና ትምህርት ምክንያት ከትንሿ አሳሳ ለቅቄ ወጣሁ። ከወጣሁ ከረጅም ጊዜ በኋላ ታላቁ የደዕዋ ሰው ሸህ ጀማልም ወደ አኺራ መሄዳቸውን ሰማሁ። የዚያን ጊዜ ፍሬያቸው የነበሩ ሰዎችን ዛሬም ድረስ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ጠንከረው ሳያቸው እጅጉን ደስ ይለኛል። አሁን እዚያ አካባቢ ያለውን የዲን ሁኔታ በጥልቀት አላውቅም። ጉዳዩን ያነሳሁበት ዋናው ምክንያት ከፍ እያላችሁ ስትሄዱ ዲናዊ አቋማችሁና ጥንካሬያችሁ ሊወርድ ስለሚችል በልጅነትም ሆነ በወጣትነት ዕድሜያችሁ አቅማችሁንና ጊዜያችሁን አሟጣችሁ ተጠቀሙ ለማለት ነው። ከልጅነት ጀምሮ ከአላህ ጋር የኖረ በአላህ ፈቃድ ምሽቱም ላይ አይበላሽም። የዲን እርሾ ትንሽም ቢሆን ብዙ ነው በረከት አለው።

ከፍ እያሉ ሲሄዱ ዱንያ አጀንዳዋ ብዙ ነው። ለዲን ከሚኖረን ጊዜ ይልቅ የዱንያ ሩጫችን ይበዛል። የዱንያ ላይ ዕድሜ ከልጅነት እስከ ሀልፈት መሆኑን እንዳትረሱ። ነገ ምንዳ የምናገኘውና የጀነት አሊያም የጀሀነም የምንባለው የምድር ላይ ሙሉ እንቅስቃሴያችን ተደምሮ ነው። መልካምና መጥፎው ሥራችን ተመዝኖ ነው ውሳኔ የሚሠጠን። መልካምነታችን ሚዛን ይደፋ ዘንድ ከፍተት በሚኖረን የወጣትነት ጊዜ ውስጥ በርትተን እንሥራ።

አሁን ላይ በተለይ ከዲን አንፃር ፈተናው በዝቷል። ዲን በየአካባቢው መልኩን የለወጠ ይመስለኛል። ሁኔታዎችም የተለዋወጡ ይመስላሉ። ያለፈውና የዛሬው ትውልድ አሳቤም የተለያየ ሆኗል። ፖለቲካና ዲኑም ተቀላቅሏል። በፖለቲካው ትኩሳት ምክንያት ዲናዊ እንቅስቃሴው ተዳክሟል። ዛሬ ላይ ወጣቶችን ማሳመን ይቸግራል። መደማመጥ ከባድ ሆኗል። ብዙዎች ውሸጉበር ውስጥ ገብተዋል። ቁጭ ብሎ እንደድሮው ለአንድና ሁለት ሰዓታት ደዕዋ ለማዳመጥ ትልቅ ትዕግስት ይጠይቃል።

በርግጥም ጊዜና ዘመኑ በተጨባጭ ተለውጧል። ዛሬ ላይ ትከከል ይሁን ኢይሁን ሳይጨነቅ "ራሴን የቻልኩ ነፃ ነኝ" ባይ በመብዛቱ ምክንያት ይመስለኛል ምክር

ሚቀበል ጠፍቷል። ሙስሊም ሆነው ከሃይማኖታዊ መልዕክቶች ጋርም ሙግት ሚገጥሙና ከዚያም አልፈው የሚዳፈሩ ጭምር ተበራክተዋል። የሆነ ጊዜ አንድ ወንድማችን በአንድ መስጊድ ላይ ደዕዋ ለማድረግ ተነሳ። በዒልሙ ደህና የሚባል ሰው ነበር። ኢማሙን አስፈቀደና ከሰዎች ፊት ቆመ። ማይኩን ጨበጠ። ለጀማዓው ሰላምታ አቅርቦ፣ አላህና ካመሰገነና በነቢዩም ላይ ሰለዋት ካወረደ በኋላ ዲስኩሩን ራሱን በሚያስተናንስ ዐረፍተነገር "እኔ ከናንተ በላይ አውቂ አይደለም፤ ግን..." ብሎ እንደጀመረ ከጀማዓው መሃል አንድ ሰው አጉረመረመ። "ከኛ በላይ ካላወቅከማ ቁጭ በል ምን ታረግልናለህ! እኛ እኮ ልናዳምጥህ እዚህ የተቀመጥነው ከኛ በላይ ታውቃለህ ብለን ነው።" አለ። በዚህን ጊዜ ዳዒው ወዳጄ ተደነጋገረ። የሚናገረው ጠፋው። ለውዬው ግን በቆመበት ትቶት ወጣ።

ስብከት ጠላሁ፣ ወሬ ጠላሁ፣ ምክር ጠላሁ... ይላል አንድ ወዳጄ በተደጋጋሚ። ሃሳብ እንጂ ምክር አይመቸውም። ራሱን ችሎ የሚኖር፣ የሚነገረውን ሁሉ የማይቀበል፣ የአስተምህሮዎችን እውነታነት ጊዜ ወስጄ ካላረጋገጥኩ የሚል ዓይነት ሰው ነው። በዚህ መልኩ የራሱን የሕይወት መስመር ያስቀመጠ ይመስላል። በርግጥ ሰው ሁሉ እንደኔ ያስብ ማለት ይከብዳል። ግና ሁሌም ቢሆን የፈጠረኝ ጌታ የአላህ ድጋፍ የሚያስፈልገኝ ሚስኪን ነኝ ብዬ አስባለሁ። ወደርሱ ካልተጠጋሁ እወድቃለሁ። በሱ ለማመን ምክንያት እፈልጋለሁ እንጂ ከርሱ ነገሮችን አልፈለፍልም።

'ሰው በእንጀራ ብቻ እንዴት ይኖራል?!' የሚል ግርምት አዘል ጥያቄ አለኝ። ሰው ያለ መንፈሳዊ ጎኑ መኖሩ አይከብደውም ወይ? ፍጥረታት ያለ መለኮታዊ መልዕክት እንዴት መኖር ይቻላቸዋል? እንዴትስ ያድጋሉ፤ ያብባሉ? ሰው ለሥጋው ጠግቦና አትርፎ ነፍሱን ቢጎዳና ቢያጎሳቁልስ ምን ይጠቀማል? ሰው የፈጠረው ጌታ እያለ እንዴት ራሴን የቻልኩ ነፃ ነኝ ብሎ አፈንግጦ እደጅ ያድራል? ሁላችንም ባለቤት አለንና ከሱ በሚደርሰን መመርያ ብቻ ነው ሰው የምንሆነው ብዬ አምናለሁ። ከዚህ ውጭ ያለ ድፍረት በርግጥም ለከሰረት ነው።

ስብከት ነው ነፍስ የሚዘራብኝ፤ ደዕዋ ከተዘናጋሁበት ማንቂያዬ ነው፤ የረሳሁትን አስተዋሽ ነው፤ ከፍ አሊያም ዝቅ ስለማለቴ ራሴን መገምገሚያዬ ነው፤ ያለሁበትን ማያ መስተዋቴ ነው። የጀርባ አጥንታችን የቆመው ከሰማዩ ዓለም በሚቀዳው መልዕክት ነው። መካሪዎች ሰዎችም ሆኑ መጽሐፎች ባይኖሩ ኖሮ ቆመን ለመሄድ ጥንካሬ ባላገኘን ነበር፤ እንደ ልብስ ሁሉ ባረጀን፤ ተተልትለን ባልለቅንም ነበር። ከወደቅንበትም ባልተነሳን ነበር።

ግና ሰባኪ አሊያም መካሪ ሲባል መልአክ እንዳልሆነ ይታወቅ ጎበዝ። መካሪም ሆነ ዳዒ የአቅሙን ያህል የሚታትር የሚፍጨረጨር፣ ለራሱና ለሌሎች መልካምነት ገጉት ያለው ሰው ነው። እሱ እንደማንኛውም ሰው ሁሉ ሥራቱ ሥጋ ነው። የሚመክረውን ሁሉ ፍፁም በሆነ መልኩ ይኖርበታል ማለት አይደለም። ባይሆን በሚመክረው ነገር ራሱንም ሆነ ሌሎችን ይጠቅማል። ሰው ሌላውን ሲመክር ይመክራል፤ ሌሎችን ሲያስታውስ ራሱንም ያረጥባል -የቀልብ እርጥበት። በተረፈ ሁሉም ስንጥቅና ሰባራ ነው። ምክርም ሆነ ማስታወስ የማያስፈልገው ማንም የለም። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቁርአን በርሳቸው ላይ ወርዶ ሳለ ከሌላ ሰው ማድመጥን ይወዱ ነበር።

No one is perfect everybody is injured

No one is original everybody is fake

"አይዟችሁ፣! አታስቡ፣ አትዘኑ፣ አትጨነቁ..." ሲል ሲመክር ኖሮ በመጨረሻም በጭንቀት ተቃጥሎ የሞተ ስንት የሥነልቦና ባለሙያ አለ መሠላችሁ!። ሰላሳ የስኬት መንገዶች ብሎ መጽሐፍ ጽፎ አንድም ስኬት ሳያስመዘግብ ዓለምን ጥሎ የሄደም ብዙ ነው። ይህ ነገር ሐራም ነው፣ ያ ነገር ክልክል ነው ሲል ሲሰብክ ሲቆጣ ሲነድ ቆይቶ በመጨረሻም ተዘፍቆበት ያየነውም በርካታ ነው። ኒቃብ አንጂ ሒጃብ ልብስ አይደለም ብላ አጣጥላ፣ አጥብቃ ስትከራከር ከርማ፣ በመጨረሻም እሷ ራሷ ኒቃቧን አውልቃ የጣለች አንዲት እህት ትዝ አለችኝ። እንዴት ይደረብባታል ብሎ ጦዞ፣ ደሙ ፈልቶ ገንፍሎ፣ ጓላ ላይ እሱ ራሱ ሁለት ሦስት ያገባም አጋጥሞናል በሐያታችን። ፍቺ መፍትሄ አይሆንም ብሎ ነቅፎ፣ ሌሎችን ተችቶና ሰድቦ ንቆ፣ እሱ ራሱ የፈታስ ቀላል ነው እንዴ?! ሆ!! የዝሙትን ፀያፍነት እያስተማረ ዝሙት ላይ የሚወድቅ፣ የሚንበጫረቅ ነፍ እኮ ነው ጎበዝ!። ሶብር አድርግ ታገስ ብሎ ያቀፈና የደገፈስ ስንቱ በሱ ላይ ደርሶ ባየው ጊዜ ለወዳጅ ዘመድ ያስቸገረስ ብዙ አይደል እንዴ?!

አናም ወዳጆቼ ለጊዜው አየኖርን ያለነውን አናውቅ ይሆናል። ምን ሆነን እንደምንሞት ግን አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው የሚያውቀው። እሱ እንዲሰትረንና እንዲያፀናን እንለምነው።

አናም ሰውን ተዉ፤ የፈጣሪያችሁን ቃል አንጂ ሰውን አትዩ። እሱን ብሎ መካሪ፣ እሷን ብሎ አስተማሪ... እሱ ራሱ እንዲህ ሆኖ... እንዲያ ሆና... አትበሉ።

አላህ ነው እንጂ ሰውማ ይንሸራተታል፣ ይወርዳል፣ ይደከማል፣ ይሰንፋል፣ ይለወጣል፣ ራሱን ያዋርዳል።

አላህ ይጠብቀን፤ ወደ ራሳችን ብቻ የምንመለከት ያድርገን።

ማስታወሻ

ከሰው ጋር ለመቀጠል ...

የሆነ ቀን ሌሊት የምእመናን መሪ አምስተኛውና ደጉ ኸሊፋው ዑመር ኢብን ዐብዱልዐዚዝ (ረ.ዐ) ከአጃቢዎቻቸው ጋር ወደ መስጊድ ገቡ። ወደ መስጊዱ ሲዘልቁ የኸሊፋው እግሮች ሳያስተውሉ አንድ መስጊዱ ውስጥ የተኛን ሰው ረገጡ። ሰውየውም ብድግ አለና በቁጣ ድምጽ-

«ኣብድ ነህን?» አላቸው።

ኸሊፋውም ነገሩን ቀለል አድርገው «አይ አይደለሁም» አሉትና ሄዱ።

በሆነው ነገር አጃቢዎቻቸው ምቾት አልተሰማቸውም። ከሰውየው የሰሙት ነገር በጣም ተናደዱና አደብ ሊያስይዙት አሰቡ፡-

«የምእመናን መሪ ሆይ! ይህ ሰው እንዴት ቢዳፈር ለርስዎ እንዲህ ዓይነት ቃል ይናገራል!?» አሏቸው።

ኸሊፋው፡- «ምን የተከሰተ እንግዳ ነገር አለ ብላችሁ ነው ጓዶቼ! ‹አንተ አብድ ነህን?› ብሎ ጠየቀኝ። እኔም ‹አይ አይደለሁም› ብዬ መለስኩለት። ይኸው ነው። ሌላ ምንም የተፈጠረ አዲስ ነገር የለም!» አሏቸውና ነገሩን አብርደው ጉዟቸውን ቀጠሉ።»

ይህ እንደ ንጉሥ ከሚፈራ አሚር የወጣ ቃል ነው። ግና ንጉሱ ራሱን እንደማንኛውም ሰው የሚመለከት ነበር።

ሕይወት ከሰው ጋር መኖር ናት፤ በግራ ቀኟ፣ ከኋላ ፊቷ ከሰው ጋር እየታከከን ነው የምንኖረው። ዛሬ ላይ ከሰው ጋር በሰላም ለመዋል ለማደር፤ ብሎም ዱንያን ለመዝለቅ የዚህ ዓይነቱ ባህሪ ያስልጋል። በተለይ የዘመኑ ሰው ሲበዛ ብሦተኛ ሆኗል። በትንሽ በትልቁ ይነጫነጫል፤ ይቆጣል። አንድ ሰው ብሦተኛ መሆኑን ከተረዳን ከሱ ጋር እሰጥ አገባ መግባት ነገሩን ማባባስ ነው የሚሆነው። ገላጋይም ለመገላገል፣ ተመልካችም ለመፍረድ ይቸገራል። ያ ከመሆኑ በፊት ራስን መያዝ፣ ነገሮችንም ቀለል አድርጎ

መመልከት፣ የማንቋቋመው ግንፍል ግንፍል የሚል ባህሪ ካለብን ደግሞ በተቻለ መጠን ከሰው ላለመነካካት መራቅ አስፈላጊ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተነካሁ ብሎ አብሪተኛ ከመሆንና ከመሰል ባህሪ ለመራቅ መታገል አለብን። በትንሽ በትልቁ መናደድና ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት፣ ግጭት ውስጥ ለመግባት መንደርደር የሙስሊም ባህሪ አይደለም። ሙስሊም ቁጣውን በመዋጥና ነገሮችን በመቻል ይታወቃል። በማያስቆጣ ነገር መቆጣት የመሃይማን ባህሪ ነው። ሙስሊም ከሰው በተለየ መልኩ ለራሱ የሚሠጠው ክብር የለም። አይደለም በስህተት አውቀው ለነኩትም ምክንያት ሰጪ ነው፣ ታጋሽ ነው፣ ይቅር ባይ ነው፣ አላፊ ነው። በትንሽ በትልቁ ነገሮችን ማጋጋል፣ ተነካሁ! ተደፈርኩ! ብሎ መዝለል ማለት የኩራት ምልክት ይመስላል። ነገረኛነትም ይመስላል። አፍንጫችን ላይ ካለች ቁጣ አላህ ይጠብቀን። ከኩራትና ንዴትም ያርቀን። መልካም ባህሪንም አስፍቶ ይስጠን።